OFFICE OF ARTS & CULTURE
CITY OF SEATTLE

# የአርቲስትስ አት ዘሰንተር (Artists at the Center) የ2023-2024 መመሪያዎች

## *የይዘት ማውጫ (ወደዚያ ዘርፍ እንዲወሰድዎት ከዚህ በታች ያለውን አማራጭ ጠቅ ያድርጉ):*


1. የድጋፍ ገንዘብ ስጦታ አጠቃላይ እይታ
   a. የድጋፍ ገንዘብ ስጦታ ዓላማ
   b. ብቁነት/ መስፈርቶች
   c. የገንዘብ ድጋፍ
   d. የግምገማ መስፈርቶች
   e. የጊዜ መስመር
2. የማመልከቻ አጭር መግለጫ እና አካላት


## *የድጋፍ ገንዘብ ስጦታ አጠቃላይ እይታ*

አርትስ አት ዘ ሰንተር የሲያትል የስነ ጥበባት እና ባህል ጽሕፈት ቤት እና የሲያትል ማእከልየብዙ ዓመታት ትብብር ሆኖ ከ Uptown Arts & Culture Coalition እና በሲያትል ማእከል ግቢ ዙሪያ ካሉ ማህበረሰቦች ዘንድ ድጋፍን ያገኛል። ይህ ፕሮጀክት ከ2021 ጀምሮ፣ ከ Climate Pledge Arena እና Seattle Kraken በተገኘ የ10-ዓመት የማህበረሰብ ጥቅም ስጦታ መቋቋም ችሏል።

አርቲስትስ አት ዘ ሰንተር በሲያትል ማእከል ዓመቱን ሙሉ ብቅ-ባይ ትርኢቶችን ማዘጋጀት እና ማቅረብ እንዲችሉ ለግለሰብ አርቲስቶች፣ ቡድኖች፣ እና ድርጅቶች የገንዘብ ድጋፍ ያደርጋል። የኪነ ጥበባዊ ዘውጎች ሙዚቃን፣ ዳንስን፣ ቲያትርን፣ ሠርቶ ማሳያዎችን፣ እና የባለብዙ የሙያ ዘርፍ ሥራዎችን ሊያካትቱ ይችላሉ። ክንዋኔዎች በጥቅምት 2023 እና በመስከረም 2024 መካከል ቀጠሮ ይያዝላቸዋል። የተመረጡ ተሳታፊዎች እንደ የአርቲስት/የቡድን መጠን እና የወሰን ውስብስብነት ላይ በመመስረት የ$2,000 ዶላር፣ $4,000 ዶላር፣ ወይም $6,000 ዶላር የገንዘብ ድጋፍ ያገኛሉ። ከአሁኑ ወቅት ከ(2022-2023) የድጋፍ ተሸላሚዎች ለ2023-2024 የውድድር ዘመን ለማመልከት ብቁ አይደሉም።

**መረጃ:** እባክዎትን እነዚህን ተዘውትረው የሚጠየቁ ጥያቄዎችን ይመልከቱ፣ ወይም በማዕከሉ ያሉ አርቲስቶች ፕሮጀክት ስራ አስኪያጅ፣ አሌክስ ሮዝ (Alex Rose)ን በ (206) 459-6517 ወይም alex.rose@seattle.gov ያግኙ።

| **ማመልከቻ** | **የሚከፈተው** |
|---|---|
| ማመልከቻው በመስመር ላይ (ONLINE) ይገባል።<br><br>ማመልከቻው በFLUXX ላይ በሲያትል ከተማ የድጋፍ ስጦታ ድህር መግቢያ በኩል በ https://seattle.fluxx.io/user_sessions/new ላይ ይገኛል | ማክሰኞ፣ ግንቦት 16 ቀን 2023፣ ጥዋት 10:00 (ፓስፊክ)<br><br>**የመጨረሻ ማስረከቢያ ቀን**<br><br>ማክሰኞ፣ ሰኔ 27 ቀን 2023፣ ከምሽቱ 5 ሰዓት (ፓስፊክ) |

| | |
|---|---|
| የኮምፒውተር ወይም የኢንተርኔት አገልግሎት መዳረሻ ከሌለዎት፣ ሰራተኞችን በተቻለ ፍጥነት ያግኙ። | |
| **የመረጃ ክፍለ-ጊዜዎች:**<br>**ስለ ፕሮግራሙ እና እንዴት ምርጥ የሆነ ማመልከቻ ማስገባት እንደሚችሉ አጠቃላይ እይታ ይቀበሉ።**<br><br>**የመረጃ ክፍለ-ጊዜ 1 (ድብልቅ)**<br>ሐሙስ፣ ሰኔ 1፣ ከሰአት ከ1-2<br>በአካል: ሲያትል ሴንተር አርሞሪ በተሰኘው ህንጻ<br>ምናባዊ: Webex<br>**እባክዎን ምላሽ ይስጡ** | **የመረጃ ክፍለ-ጊዜ 2 (ድብልቅ)**<br>ቅዳሜ፣ ሰኔ 17፣ ጥዋት ከ10 - 11<br>በአካል: ሲያትል ሴንተር አርሞሪ በተሰኘው ህንጻ<br>ምናባዊ: Webex<br>**እባክዎን ምላሽ ይስጡ** |

**ለእርዳታ፣ የሚከተለውን ያግኙ:**

- ***ማመልከቻ ወይም መዳረሻ*** የአርቲስትስ አት ዘ ሰንተር ፕሮጀክት ሥራ አስኪያጅ አሌክስ ሮዝን በ (206) 459-6517 ወይም alex.rose@seattle.gov ያግኙ
- ***የመስመር ላይ የቴክኒክ ድጋፍ*** የአስተዳደራዊ ልዩ ባለሙያ የሆነውን ማርሾን ዎከር (Marshonne Walker)ን በ marshonne.walker@seattle.gov ያግኙ
- **የአሜሪካ የምልክት ቋንቋን ጨምሮ፣ በእርስዎ ቋንቋ ሊያናግሩዎት የሚችሉ አስተርጓሚዎች አሉን።** ብቻ ይደውሉልን እና እርስዎ የሚናገሩትን ቋንቋ ይንገሩን። አስተርጓሚ እንዲቀላቀለን ስንደውልለት ለአጭር ጊዜ ይጠብቃሉ።

## ***የድጋፍ ገንዘብ ስጦታ ዓላማ***

በማዕከሉ ያሉ አርቲስቶች የተነደፈው በUptown Arts & Cultural District ውስጥ ያሉ ኪነ ጥበባትን እና ባህላዊ ልምዶችን በማስፋት ታዳጊ እና የተመሰረቱ አርቲስቶችን ወደ ታደሰ የሲያትል ማዕከል ግቢ በማስተዋወቅ ንቁ የኪነጥበብ ማህበረሰባችንን ለመደገፍ ነው። የተመረጡ አርቲስቶች የከተማዋን የባህል ብዝሃነት የሚያንፀባርቁ እና በሲያትል ማእከል መተወን፣ የቴክኒካዊ ማምረት ድጋፍ ለመደሰት፣ ከአዳዲስ ታዳሚዎች ጋር ለመገናኘት እና ችሎታቸውን ለማሳየት ልዩ እድል አላቸው። ወደ ግቢው የሚመጡ ጎብኚዎች እና የአካባቢው ተጎራባች አመቱን ሙሉ በሚያስደንቅ እና በሚያስደስቱ ብቅ-ባይ ትርኢቶች ይጠቀማሉ።

## ***ብቁነት/ መስፈርቶች***

የሚከተሉትን መመዘኛዎች ካሟሉ ለዚህ ስጦታ ለማመልከት **እርስዎ ብቃት አልዎት**:

- በሲያትል ውስጥ የሚገኙ/ የሚቀመጡ ወይም በመደበኛነት ሥራ የሚያቀርቡ፣ ግለሰብ አርቲስት፣ ድርጅት፣ ወይም በማህበረሰብ ላይ የተመሰረተ ቡድን ከሆኑ።
  - ዝቅተኛ ገቢ ያላቸው፣ አካል ጉዳተኛ ሰዎች፣ አዲስ ሰፋሪዎች እና የስደተኛ ማህበረሰቦች፣ እና የቀለም ማህበረሰቦችን ጨምሮ በስርዓታዊ ጭቆና እጅግ የተጎዱ ማህበረሰቦችን የሚወክሉ ድርጅቶች እና አርቲስት ግለሰቦች እንዲያመለክቱ ይበረታታሉ።

- የፌዴራል የታክስ መታወቂያ ቁጥር (የማህበራዊ ዋስትና ቁጥር (Social Security Number) ፣ ITIN፣ ወይም የሰራተኛ መለያ ቁጥር) ያለዎት ሲሆን በሲያትል ከተማ ውስጥ መሰረት ያደረጉ፣ ወይም በአሁኑ ጊዜ ያለ ወቅታዊ እና በአግባቡ የሚሠራ ፕሮግራሞችን የሚያካሄዱ ከሆነ።
    - የሚያመለከቱ ቡድኖች 501(c)(3) ለትርፍ ያልተቋቋሙ መሆን አይጠበቅባቸውም፣ ወይም የፊናንስ ወኪል መጠቀም አይጠበቅባቸውም።
- ለዚህ ፕሮግራም በዓመት አንድ ማመልከቻ ብቻ ማስገባት ይችላሉ።
- ከአሁኑ ወቅት (2022-2023) ተሸላሚዎች የሆኑ ለ2023-2024 የውድድር ዘመን ለማመልከት **ብቁ አይደሉም።**

የሚከተሉትን መመዘኛዎች የሚያሟላ ከሆነ በዚህ የድጋፍ ስጦታ ገንዘብ ለማግኘት **የእርስዎ አፈጻጸም ብቁ ነው**:

- የእርስዎ አፈጻጸም ለህዝብ ነጻ እና ክፍት ይሆናል።
- ለአፈፃፀሙ የክስተት ኢንሹራንስ ይኖርዎታል።
- አፈፃፀሙ 90 ደቂቃ ወይም ከዚያ በታች ይቆያል።

## ***የገንዘብ ድጋፍ***

የሽልማቶች ገንዘብ ድጋፍ ለአርቲስት ክፍያዎች፣ ለግብይት እና ለማስተዋወቂያ ክፍያዎች፣ ለፕሮጀክት ሥራ ማስኬጃ እና የሰራተኞች ወጪዎች፣ ለአቅርቦቶች፣ ለመሳሪያ ኪራዮች ወይም ሌሎች ከምርት ጋር ለተዛመዱ ወጭዎች፣ ለአስፈላጊ ኢንሹራንስ፣ እና ከ10% ያልበለጠ ከምግብ ጋር ለተዛመዱ ወጪዎች ጥቅም ላይ ሊውል ይችላል። በድጋፍ ስጦታ የፕሮጀክት ሥራ አስኪያጁ በቅድሚያ ሲጸድቅ ምናልባት ተጨማሪ ወጪዎች ሊፈቀዱ ይችላሉ።

አመልካቾች ለሚከተሉት የገንዘብ ድጋፍ ደረጃዎች ማመልከት ይችላሉ:

- ለ2,000 ዶላር ሽልማት (በተለምዶ 1-2 ተዋናዮች)፣ እና $600 ዶላር በአይነት የምርት ድጋፍ
- የ4,000 ዶላር ሽልማት (በተለምዶ ከ3-5 ተዋናዮች)፣ እና $1,100 ዶላር በአይነት የምርት ድጋፍ
- የ6,000 ዶላር ሽልማት (በተለምዶ 6+ ፈፃሚዎች)፣ እና $1,600 በአይነት የምርት ድጋፍ

ይህ የገንዘብ ድጋፍ ለሚከተሉት ጥቅም ላይ ሊውል አይችልም:

- ለህዝቡ ተደራሽነት የሌላቸው እና ነፃ ያልሆኑ ክስተቶች
- ሃይማኖታዊ አገልግሎቶች
- የድጋፍ ገንዘብ ማሰባሰብ ዋና ዓላማ ያደረጉ ዝግጅቶች ወይም አቀራረቦች
- ስጦታዎች
- ከፕሮጀክቱ ጋር በቀጥታ ግንኙነት ለሌላቸው የድርጅቶች አስተዳደራዊ ወጪዎች
- የመሳሪያ/መገልገያ ወይም የሶፍትዌር ግዢ

## ***የግምገማ መስፈርቶች***

ለፕሮግራሙ የቀረቡ የምክር ሀሳቦች በሚከተሉት መስፈርቶች ይገመገማሉ:

- **የሙያ እድገት**: ማመልከቻው አርቲስቱን/ ቡድኑን ከአዳዲስ ታዳሚዎች ጋር ያስተዋዉቃል፣ የምርት ድጋፍ ያደርጋል፣ እና ተሰጥኦዋቸውን ልዩ በሆኑ ቅንብሮች በሲያትል ማእከል በማሳየት ተጠቃሚ እንዲሆኑ እድል ይሰጣል።
- **ስኬታማነት**: አመልካቹ አፈፃፀሙን/ስራውን በተግባር ላይ ለማዋል ያለውን የማደግ ልምድ ወይም አቅም በምሳሌ ያስረዳል (ልምድ ካላቸው አጋሮች ወይም ተባባሪዎች እርዳታ ማግኘትን ጨምሮ)።
- **ጥበበኛነት**: ማመልከቻው ታዳሚዎች እንዲሆኑ ከታቀዱት ጋር የሚስማማ፣ አሳማኝ እና ትክክለኛ የኪነጥበብ/የባህላዊ ልምድን ያቀርባል።
- **ባህላዊ አግባብነት**: ማመልከቻው የፈጠራ ሰዎች ከጥቁር፣ ከቡናማ፣ ከሀገሬው ተወላጅ፣ ከእስያ እና ከዲያስፖራ፣ አዲስ ሰፋሪዎች፣ ስደተኛ፣ እና ከሌሎች ያልተገለገሉ እና ከተገቢው በታች የተገለገሉ ማህበረሰቦችን ቅድሚያ ይሰጣል።

## ***የጊዜ መስመር***

ይህ የጊዜ መስመር ግምታዊ ነው እና ሊለወጥ ይችላል።

- **ግንቦት 16 ቀን 2023 (ጥዋት 10)** : ማመልከቻ ይከፈታል
- **ሰኔ 27 ቀን 2023 (ከምሽቱ 5 ሰዓት)** : ማመልከቻ ይዘጋል
- **ከሐምሌ - ነሐሴ መጀመሪያዎቹ 2023:** የተወያዮች ግምገማ
- **ነሐሴ አጋማሽ 2023:** በARTS አመራር የተገመገመ የገንዘብ ድጋፍ የምክር ሀሳቦች
- **ነሐሴ መጨረሻ 2023:** አመልካቾች ስለ የገንዘብ ድጋፍ ውሳኔዎች ማሳወቂያ ይሰጣቸዋል
- **መስከረም 2023:** የተሸላሚ ማስተዋወቂያ እና ኮንትራት ማድረጊያ
- **ከጥቅምት 2023 - መስከረም 2024:** በማዕከሉ ያሉ አርቲስቶች የትወና ክንዋኔአቸውን ያቀርባሉ።

## ***የማመልከቻ አጭር መግለጫ እና አካላት***

*የሲያትል ከተማ የድጋፍ ስጦታ ማመልከቻውን በ*[**FLUXX**](#) *ስርዓት ይጠቀማል። እስካሁን ድረስ ይህንን አድርገውት ካልሆነ፣ ወደ ማመልከቻው ከመድረስዎ በፊት አንድ አዲስ አጠቃላይ የራስዎን መገለጫ መፍጠር ያስፈልግዎታል።*

- **የግንኙነት እውቂያ/ ፊስካል ስፖንሰር ኢንፎርሜሽን:** ይህ ክፍል በመመዝገቢያው የግል መገለጫ ውስጥ አስቀድሞ ያልተጠየቀ ለዚህ ማመልከቻ የተለየ ሆኖ ነገር ግን ተጨማሪ የግንኙነት እውቂያ መረጃን ይሰጣል።
- **የማመልከቻ ጥያቄዎች/ የፕሮጀክት መረጃ:** የነዚህ ጥያቄዎች አላማ ስለ እርስዎ ክስተት/ ፕሮጀክት፣ ስለሚያገለግለው ማህበረሰብ እና አንዳንድ ስለ ራስዎ ያለፉት ሁኔታዎችን ለማካፈል ነው።
    1) **የአርቲስት/ድርጅት ድር ጣቢያ ወይም ማህበራዊ የሚዲያ አገናኝ**
    2) **የሙያ ዘርፍ:** ለምክር ከቀረበ ፕሮጀክት ውስጥ አንዱን የኪነ ጥበባዊ የሙያ ዘርፍ ይምረጡ
    3) **የፕሮጀክት ርዕስ**

4) **የፕሮጀክት ማጠቃለያ**: በጥቂት ዓረፍተ ነገሮች፣ እባክዎን በሲያትል ማእከል ሊያቀርቡት የሚፈልጉትን ብቅ ባይ ተውኔታዊ አፈጻጸም ያብራሩ። የታዳሚው ልምድ ምን ይሆን? የኪነት አፈጻጸም ርዝማኔን፣ የአርቲስቶችን ብዛት፣ ዘውግን፣ አዲስ ወይም እንደገና የተገጠመ ሥራ፣ የቴክኒክ ፍላጎቶችን፣ እና ሌላ የሚሰማዎትን ማንኛውንም ለግንዛቤ ጠቃሚ የሆነውን ነገር ያካትቱ ። (ቢበዛ 500 ቃላት)
5) **ዳራ:**እርስዎ ማን እንደሆኑ፣ የሙያ ችሎታ ዘርፎችዎን፣ ቁልፍ ስኬቶችዎን፣ እና ክንውኖችን ወይም ልምድ ያገኙባቸው ዝግጅቶችን እና ክስተቶችን፣ በተለይም በኪነታዊ ጥበብ የሙያ ዘርፍዎ ውስጥ በአጭሩ ያብራሩ። (ቢበዛ 250 ቃላት)
6) **የሽልማት ምድብ ምርጫዎች**: ለምክር ያቀረቡትን አፈጻጸም በተሻለ ሁኔታ በማንጸባረቅ፣ የመጀመሪያ፣ ሁለተኛ፣ እና የመጨረሻ የምርጫ ምድብዎን ያመልክቱ።
    - አነስተኛ (1-2 ተዋናዮች): የ2,000 ዶላር ሽልማት፣ እና እስከ $600 ዶላር የሚደርስ በምርት የዓይነት ድጋፍ
    - መካከለኛ (ከ3-5 ተዋናዮች): የ$4,000 ዶላር ሽልማት፣ እና እስከ $1,100 ዶላር በምርት የዓይነት ድጋፍ
    - ትልቅ (6+ ተዋናዮች): የ6,000 ዶላር የድጋፍ ሽልማት፣ እና እስከ $1,600 ዶላር በምርት የዓይነት ድጋፍ
7) **የመርሐግብር ምርጫዎች**: ይህም ለማከናወን ያለዎትን ብቃት በማንጸባረቅ፣ የመጀመሪያ፣ የሁለተኛ፣ የሦስተኛ እና የመጨረሻ የሩብ ዓመት ምርጫዎን ያመልክቱ።
    - ከጥቅምት - ታህሳስ 2023
    - ከጥር - መጋቢት 2024
    - ከሚያዝያ - ሰኔ 2024
    - ከሐምሌ - መስከረም 2024

- **የስነ-ሕዝብ መረጃ:** ይህ **እንደ ማመልከቻዎ አካል ሆኖ አይገመገምም** ነገር ግን ፕሮግራሞቻችንን የበለጠ ፍትሃዊ እኩልነት ያለው ለማድረግ መስራታችንን መቀጠል እንድንችል ይልቁንም ARTS በፕሮግራሞቻችን ስለምንደርሳቸው ማህበረሰቦች የበለጠ እንዲያውቅ ለመርዳት ነው። ምላሾች እሰጣለሁ ብለው ከመረጡ ነው፣ ነገር ግን አመልካቾች ወደ ቀሪው ማመልከቻ ከመቀጠላቸው በፊት መጠይቁን ከምላሾቹ ጋር ወይም ያለ ምላሾቹ ማቅረብ/ማስረከብ አለባቸው።